SWEDISH
Extraordinary care. Extraordinary caring.™

| | |
|---|---|
| **ርዕሰ ጉዳይ፡- የስዊዲን የጤና አገልግሎት (Swedish Health Services) የገንዘብ ድጋፍ (ልግስና የጤና እንክብካቤ) ፖሊሲ** | **የፖሊሲ ቁጥር፡-** PSJH RCM 0002 የስዊዲን የጤና አገልግሎት |
| **መምሪያ፡-**<br>የገቢ አገባብ አስተዳደር | ☒ አዲስ<br>☐ የተሻሻለ<br>☐ የተመረመረ — **ቀን፡-** 3/22/2019 |
| **አስፈፃሚ ስፖንሰር፡-**<br>Kimberly Sullivan, SVP ዋና የገቢ አገባብ መኮንን | **የፖሊሲ ባለቤት፡-**<br>Lesa Ellis, የገንዘብ ምክር አገልግሎት እና ድጋፍዳይሬክተር |
| **ያፀደቀው፡-** PSJH የዳይሬክተሮች ቦርድ | **የትግበራ ቀን፡-** 5/1/2019 |

የስዊዲን የጤና አገልግሎት እና Swedish Edmonds (“SHS” ወይም “Swedish”) ለትርፍ ያልተቋቋመ የጤና እንክብካቤ የሚሰጥ እና አገልግሎት የምንሰጠው የእያንዳንዱ ግለሰብ ጤንነት እና ደህንነት በቁርጠኝነት የማሻሻል ተልዕኮው፣ በዋና እሴቶቹ ደህንነት፣ ታካሚ ተኮር እንክብካቤ፣ አክብሮት፣ ጥንቃቄ እና ርህራሄ፣ የቡድን ስራ እና አጋርነት፣ ተከታታይነት ያለው መማር እና መሻሻል እና አመራር እና የጤና እንክብካቤ ሰብዓዊ መብት መሆኑን በማመን የሚመራ ድርጅት ነው፡፡ አዲስ የመጡ እና በህክምና አስፈላጊ የሆኑ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች የመክፈል አቅማቸው ምንም ይሁን ምን የምናገለግለው ማህበረሰብ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች በቀላሉ እንዲገኙ ማድረግ የእያንዳንዱ የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታል ፍልስፍና እና ተግባር ነው፡፡

## ወሰን፡-

ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ የሚሆነው በሁሉም የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች እና በሆስፒታሎቹ በሚሰጡ ድንገተኛ፣ አስቸኳይ እና በህክምና አስፈላጊ በሆኑ (የሙከራ ወይም የምርመራ እንክብካቤዎች ሳይጨምር) በሁሉም አገልግሎቶች ላይ ነው፡፡ በዚህ ፖሊሲ ሽፋን የሚያገኙ የስዊዲን የጤና አገልግሎቶች ሆስታሎች ዝርዝር በኤግዚቢት ኤ ሽፋን ያላቸው ተቋማት ዝርዝር ውስጥ ማግኘት ይቻላል፡፡

ይህ ፖሊሲ የሚተረጎመው በተሻሻለው የ1986 የውስጥ ገቢ ኮድ ክፍል 501 (r) ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነቶቹ ህጎች ድንጋጌ እና በዚህ ፖሊሲ መካከል ግጭት ቢፈጠር፣ ህጎቹ ገዢ ይሆናሉ፡፡

## ዓላማ፡-

የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ለገንዘብ ድጋፍ (የልግስና እንክብካቤ) ፍትሃዊ፣ የማያዳላ፣ ውጤታማ እና ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ብቁ ለሆኑ እና በስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች ለሚሰጡ በህክምና አስፈላጊ ለሆኑ ድንገተኛ አገልግሎቶች እና ለሌላ የሆስፒታል አገልግሎቶች ሙሉ ወይም ከፊል ክፍያ መክፈል ለማይችሉ ግለሰቦች የሚሰጥበትን መንገድ ለማረጋገጥ ነው፡፡

በሁሉም የፌደራል፣ የግዛት እና የአካባቢ ሕጎች መገዛት የዚህ ፖሊሲ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ፖሊሲ እና እዚህ ያሉ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ይፋዊውን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲን (‘FAP’) እና በድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ ፖሊሲ ለእያንዳንዱ በስዊዲን የጤና እንክብካቤ ባለቤትነት ስር፣ በኪራይ ወይም በእንክብካቤው ለሚንቀሳቀስ እያንዳንዱ ሆስፒታል ያካትታሉ፡፡

## ፖሊሲ፡-

ብቁ ለሆኑ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው፣ መድን ለሌላቸው እና ዝቅተኛ መድን ላላቸው ታካሚዎች ለአገልግሎት የሚከፍሉበት አቅም ያለመኖሩ በህክምና አስፈላጊ የሆኑ የድንገተኛ እና ሌላ የሆስፒታል አገልግሎት እንዳያገኙ እንቅፋት በሚሆንበት ጊዜ እና ምንም ዓይነት አማራጭ የሽፋን ምንጭ በሌለበት ሁኔታ የስዊዲን የጤና አገልግሎት ነፃ ወይም ቅናሽ የተደረገባቸው የሆስፒታል አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡ ታካሚዎች ብቁ ለመሆን በዚህ ፖሊሲ የተገለፁት የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታል ያለመድልዎ፣ ለድንገተኛ የህክምና ሁኔታዎች (በድንገተኛ ህክምና እና የሥራ ሕግ ትርጓሜ ስር የሚገኙ)፣ ካለው አቅም ጋር የተጣጣሙ፣ አንድ ግለሰብ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ቢሆንም ባይሆንም በታማኝ የድንገተኛ መምሪያዎቹ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የስዊዲን የጤና አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔዎችን ሲያደርግ በዕድሜ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በእምነት፣ በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በብሄራዊ መገኛ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታ፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ ማንነት ወይም አገላለፅ፣ በአካል ጉዳት፣ በአርበኝነት ወይም ወታደራዊ ሁኔታ፣ ወይም በሌላ ማንኛውም በፌደራል፣ በግዛት ወይም በአካባቢያዊ ሕጎች በተከለከለ ጉዳይ መነሻት መድልዎ አያደርግም፡፡

የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች ድንገተኛ የህክምና ልየታ ምርመራዎችን በመስጠት የማረጋጊያ ህክምና ያደርጋሉ ወይም ግለሰቡን ወደሌላ ቦታ ሪፈር ያደርጋሉ ወይም ማስተላለፉ በ 42 C.F.R 482.55 መሠረት ተገቢ ከሆነ ያስተላልፋሉ፡፡ የስዊዲን የጤና አገልግሎት ማንኛውንም ድርጊት፣ የመግቢያ ድርጊቶች ወይም ከድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ ድንጋጌዎች ላይ ጣልቃ የሚገቡ የዕዳ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎችን መፍቀድን የመሳሰሉ ግለሰቦች የድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ ለመጠየቅ ተስፋ የሚያስቆርጡ ፖሊሲዎችን ይከለክላል፡፡

**<u>የሲዊዲን ጤና አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞችን የሚሰጡ አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር፡-</u>** እያንዳንዱ የሲዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታል በተለይ በዚህ ፖሊሲ ሽፋን ያላቸውን እና የሌላቸውን ሀኪሞች፣ የህክምና ቡድኖች ወይም ሌሎች ባለሞያዎችን ዝርዝር ይለያል፡፡ እያንዳንዱ የሲዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታል ቅጂ ለጠየቀ ማንኛውም ታካሚ ይህንን ዝርዝር ይሰጣል፡፡ የአገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር በተጨማሪም ኦንላየን በሲዊዲን ጤና አገልግሎቶች ድረ-ገፅ ሊገኝ ይችላል፡፡ www.swedish.org.

**<u>የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት መስፈርቶች፡-</u>** መድን ላላቸውም ለሌላቸውም ታካሚዎች እና ዋስትና ሰጪዎች ድጋፉ ለታካሚዎች የሚፈቀዱ ጥቅማ ጥቅሞችን ከሚገዛበት ከዚህ ፖሊሲ እና ከፌደራል እና የግዛቱ ሕጎች ጋር የተጣጣመ ከሆነ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ በሲዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች ለሚሰጡ እንክብካቤዎች ከታካሚው ምንም ዓይነት የመሰብሰብ ሙከራ ከማድረጋቸው አስቀድ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚቀርቡ የሦስተኛ ወገን ሽፋኖች መኖር ወይም ያለመኖራቸውን ለመወሰን ሆስፒታሎቹ ምክንያታዊ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

የገንዘብ ድጋፍ የሚጠይቁ ታካሚዎች መደበኛውን የስዊዲን ጤና አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻን መሙላት ያለባቸው ሲሆን ብቁነት የሚመሰረተው እንደተገቢነቱ አገልግሎቱ መሰጠት ከጀመረበት ወይም ማመልከቻው ከገባበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡ በጊዜ ሂደት የገንዘብ ሁኔታቸው እየከፋ ከሄደ ታካሚዎች ምንም እንኳን ከዚህ በፊት ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ባያገኝም ወይም ከፊል ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም በድጋሚ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡፡ ታካሚዎች ሆስፒታል በሚገቡበት እና በሚወጡበት ጊዜ፣ የሂሳብ አከፋፈል ወይም አሰባሰብን በተመለከተ በፅሁፍ መገናኛ፣ በታካሚ ተደራሽ የሂሳብ አከፋፈል ወይም የገንዘብ አገልግሎት ቦታዎች፣ በሲዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታል ድረ-ገፅ፣ የክፍያ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ በቃል ማሳወቂያ እንዲሁም የመቀበያ እና የድንገተኛ መምሪያዎችን በመሳሰሉ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ታካዎች እና ተመላላሽ ታካሚዎች በሚገኙባቸው ቦታዎች መረጃ በመስጠት የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን በተመለከተ ለማሳወቅ እና መረጃ ለመስጠት ምክንያታዊ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ ሆስፒታል አገልግሎት በሚሰጥበት አካባቢ የሚገኙ ከአስር በመቶ በላይ የሆኑ ሰዎች በሚናገሩት ማንኛውም ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል፡፡

**<u>የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት፡-</u>** ታካምሚዎች ወይም ዋስትና ሰጪዎች ከክፍያ ነፃ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ለማግኘት በስዊዲን ጤና አገልግሎት ቢሮ በኩል ወይም በሚከተሉት መንገዶች፡ የታካሚ የገንዘብ አገልግሎቶች ምክር ሰጪ ሠራተኛ ከሆስፒታል መውጪያ ጊዜ ወይም ቀደም ብሎ ድጋፍ በመጠየቅ በተሟላ ሰነድ በኢሜይል በመላክ ወይም www.swedish.org በመጎብኘት እና የማመልከቻ ቅፁን በማውረድ እና በመሙላት ማመልከቻውን በተሟላ ሰነድ ሊጠይቁ እና ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያመለክት ታካሚ ለማንኛውም የሦስተኛ ወገን ክፍያ ምንጮችን መሞከሩን ወይም ብቁ ያለመሆኑን መመርመርን የሚጨምረውን የታካሚ ቅድመ ልየታ ይደረግለታል ፡፡

እያንዳንዱ የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታል ታካሚዎችን የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻውን ሲሞሉ የሚያግዛቸው እና የስዊዲን የጤና አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ እና በመንግሥት የሚደገፉ የመድን ፕሮግራሞችን የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆናቸውን የሚወስን ባለሞያ ይመድባሉ፡፡ ለማንኛውም ጥያቄ እና ስጋቶች ምላሽ ለመስጠት እና የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻውን ለመሙላት የትርጉም አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡

ለገንዘብ ድጋፍ ለማመልከት ብቁ የሆነ አንድ ታካሚ ወይም ዋስትና ሰጪ ለስዊዲን ጤና አገልግሎት የብቁነት መወሰኛውን ለመደገፍ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ወገን ከዝቅተኛው የፌደራል የድህነት ደረጃ በታች ሲወርድ በተገቢው የፌደራል እና የግዛት ደንቦች መሠረት በቂ ሰነዶችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

የስዊዲን ጤና አገልግሎት በዋሽንግተን የአስተዳደር ኮድ (WAC) 246-453-020፣ መሠረት የብቁነት ውሳኔ የአንድ ወገን ገቢ ከፌደራል የድህነት ደረጃ 200 በመቶ በታች መውረዱን ባወቀበት በማንኛውም ጊዜ እውቅና ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም የስዊዲን ጤና አገልግሎት በWAC 246-453-010 ላይ በተገለፀው መሠረት መጀመሪያ ላይ አቅም የሌለው ተደርጎ የተወሰነውን የታካሚው ሁኔታ ብቻ ላይ በመመስረት የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት ሊመርጥ ይችላል፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች፣ ሰነድ ላያስፈልግ ይችላል፡፡

**<u>የግለሰብ የገንዘብ ሁኔታ፡-</u>** የታካሚው ገቢ፣ የገንዘብ ሀብቶች እና ወጪዎች የታካሚው ግለሰባዊ የገንዘብ ሁኔታ በሚመረመርበት ጊዜ አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ ለገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ዓላማ፣ ዋሽንግተን ገቢ እና ቤተሰብን የሚገልጸው በ WAC 246-453-010 መሠረት ነው፡፡ የገንዘብ ሀብቶች በውስጥ የገቢ ኮድ ስር ብቁ የሆኑ የጡረታ ወይም የተዘዋወሩ የካሳ ዕቅዶችን እና ብቁ ያልሆኑ የተዘዋወሩ የካሳ ዕቅዶችን አያካትትም፡፡ የታካሚው ወይም የዋስትና ሰጪው ገቢ ከፌደራል የድህነት ደረጃ 200 በመቶ ወይም ከዚያ በታች ያነሰ ከሆነ የገንዘብ ሀብቶች ለብዉነት መወሰኛነት ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡

**<u>የገቢ ብቃት፡-</u>** የገቢ መስፈርት፣ በፌደራል የድህነት ደረጃ (FPL)፣ ለነፃ ወይም ቅናሽ ለተደረገበት እንክብካቤ ብቁ መሆንን ለመወሰን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡ ለዝርዝሩ እባክዎን ኤግዚቢት B ን ይመልከቱ፡፡

**<u>ውሳኔዎች እና ፈቃዶች፡-</u>** ታካሚዎች የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ እና አስፈላጊ ሰነዶችን ባስገቡ በ14 ቀናት ውስጥ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ብቁነት ውሳኔ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል፡፡ አንዴ ማመልከቻ ከቀረበ ለታካሚው የብቁነት ውሳኔ በፅሁፍ እስኪላክ ድረስ ልዩ የመሰብሰቢያ ጥረቶች ይገታሉ፡፡ ሆስፒታሉ ትክክል አይደለም ወይም አስተማማኝ አይደለም ብሎ ባመነበት መረጃ ላይ ተመስርቶ የድጋፍ ብቁነት ውሳኔ አያስተላልፍም፡፡

**<u>ያለመግባባትን መፍታት፡-</u>** ታካሚው የክልከላ ማሳወቂያውን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ ለሆስፒታሉ ተገቢ የሆኑ ተጨማሪ ሰነዶችን በማቅረብ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ያለመሆንን ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡፡ ሁሉም ይግባኞች ይመረመርና እና ምርመራው ክልከላውን ካረጋገጠ፣ እንዳስፈላጊነቱ እና በሕጉ መሠረት ለዋስትና ሰጪው እና ለግዛቱ የጤና መምሪያ የፅሁፍ ማሳወቂያ ይላካል፡፡ የመጨረሻው የይግባኝ ሂደት ክልከላው ለሆስፒታሉ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ ለስዊዲን የህክምና ማዕከል (Swedish Medical Center) አቤቱታ ሊላክ ይችላል፡- Corporate Business Office, 747 Broadway, Seattle, WA 98122.

**ምናልባታዊ ልገሳ:-** የሲዊዲን ጤና አገልግሎት አንድን ታካሚ ከሙሉ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ መንገድ ውጪ በሂሳባቸው ስር በሚገኝ የልግስና ማስተካከያ አገልግሎት እንዲያገኝ ሊፈቅዱለት ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች የሚደረጉት በኢንዱስትሪው እውቅና በተሰጣቸው በግልፅ በሚታዩ የገንዘብ ወይም ሌሎች መዝገቦችን የቤተሰብ ገቢ፣ የቤተሰብ ቁጥር እና የብድርና የክፍያ ታሪክን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን የገንዘብ ግምገማ በሚያደርጉ መሳሪያዎችን በመጠቀም በምናልባት ነው።

**ሌሎች ልዩ ሁኔታዎች:-** Medicaid እና ሌሎች በመንግሥት ስፖንሰር የሚደረጉ የዝቅተኛ ገቢ ድጋፍ ፕሮግራሞች ለመሳሰሉ የፌደራል የድህነት ደረጃ-ብቁ ፕሮግራሞች ብቁ የሆኑ ታካሚዎች ድሀ ናቸው ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም ፕሮግራሞቹ ክፍያ ሲከለክሉ እና መከፈል ያለባቸውን ክፍያዎች ለታካሚው በሚሰጡበት ጊዜ እንደዚህ ዓይነቶቹ ታካሚዎች ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ይሆናሉ። ተመላሽ የማይሆኑ ክፍያዎች ውጤት የሆኑ የታካሚ ሂሳቦች ለሙሉ ልግስና ወጪ ለማግኘት ብቁ ናቸው። በተለየ ሁኔታ ብቁ ናቸው ተብለው የተካተቱት ከሚከተሉት ጋር የተገናኙ ክፍያዎች ናቸው:-

- የተከለከሉ የታካሚ ቆይታዎች
- የተከለከሉ የታካሚ የእንክብካቤ ቀናት
- ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች
- የቀደሙ የህክምና ፍቃድ ክልከላዎች
- በተወሰኑ ሽፋኖች ምክንያት የሚከሰት ክልከላ

**አስከፊ የህክምና ወጪዎች:-** የስዊዲን ጤና አገልግሎት በምርጫው አስከፊ የህክምና ወጪዎች በሚገጥሙበት ጊዜ ልግስና ሊሰጥ ይችላል። እነዚህ ታካሚዎች የሚስተናገዱት በተናጠል ነው።

**ለሁሉም የገንዘብ ድጋፎች ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች ላይ የሚደረጉ የክፍያ ገደቦች:-** ከላይ ለተጠቀሱት ለማንኛውም የድጋፍ ምድቦች ብቁ የሆነ ማንም ታካሚ ከዚህ በታች እንደተገለፀው ከአጠቃላይ ክፍያው "አጠቃላይ ክፍያ የሚከፈልባቸው ሂሳቦች" (AGB) በላይ ላሉ ክፍያዎች በግል ኃላፊነቱን አይወስድም።

**ምክንያታዊ የክፍያ ዕቅድ:-** አንድ ጊዜ አንድ ታካሚ የከፊል የገንዘብ ድጋፍ ፍቃድ ያገኘ ሆኖ ነገር ግን አሁንም የሚከፈል ሂሳብ ካለበት የሲዊዲን ጤና አገልግሎት የክፍያ ዕቅድ ማስተካከያ ይደራደራል። ምክንያታዊ የክፍያ ዕቅድ ታካሚው በገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻቸው ላይ ለዘረዘሩት አስፈላጊ የኑሮ ወጪዎች የሚደረጉ ተቀናሾችን ሳይጨምር ከታካሚው ወይም ከቤተሰቡ ወርሃዊ ገቢ ከ10 በመቶ ያልበለጡ ወርሃዊ ክፍያዎችን ያካትታል።

**ክፍያዎች እና አሰባሰቦች:-** ቅናሾች ከተተገበሩ በኋላ በታካሚዎች ወይም በዋስትና ሰጪዎች ያልተከፈሉ ማንኛውም ሂሳቦች የሚኖሩ ከሆነ እንዲሰበሰቡ ሊተላለፉ ይችላሉ። ያተከፈሉ ሂሳቦችን የመሰብሰብ ጥረቶች ያላለቀ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ብቁነት የመጨረሻ ውሳኔን ያስቆማል። ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ሁለት ጉዳዮች አስቀድሞ ሰብሳቢ ድርጅቶች ማንኛውም የተለዩ የስብሰባ ድርጊቶችን እንዲያደርጉ የስዊዲን ጤና አገልግሎት አይፈቅድም እራሱም አያደርግም:- (ሀ) ታካሚው ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆኑን ለመወሰን ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ፤ ወይም (ለ) የታካሚው የመጀመሪያ ሂሳብ መጠየቂያ ከተላከ 120 ቀናት በኋላ። የስዊዲን ጤና አገልግሎት ታካዎች ያለባቸውን ክፍያ አከፋፈል እና የመሰብሰቢያ አሰራሮችን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በእያንዳንዱ የስዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች የመመዝገቢያ ዴስክ ወይም ከዚህ በታች ባለው የድረ-ገፅ አድራሻ በነፃ የሚገኘውን የስዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች ፖሊሲ ይመልከቱ:- www.swedish.org.

**የታካሚ ተመላሽ ገንዘቦች:-** አንድ ታካሚ ወይም ዋስትና ሰጪ ለአገልግሎቶች ክፍያ ከከፈለ በኋላ ለነፃ ወይም ለቅናሽ እንክብካቤ ብቁ መሆኑ ከተወሰነ በገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ብቁነት ጊዜ ከእነዚያ አገልግሎቶች ጋር በተገናኘ የተፈጸመ ከክፍያ ግዴታው የሚበልጥ ማንኛውም ክፍያ በግዛቱ ደንቦች መሠረት ተመላሽ ይሆናል።

**ዓመታዊ ግምገማ:** ይህ የProvidence የገንዘብ ድጋፍ (ልግስና የጤና እንክብካቤ) ፖሊሲ በተመረጠ የገቢ አሰራር አመራር በየዓመቱ ይሻሻላል።

## የተለዩ ሁኔታዎች:-

ከላይ ያለውን ወሰን ይመልከቱ።

## ትርጓሜዎች:-

ለዚህ ፖሊሲ ዓላማዎች የሚከተሉት ትርጓሜዎች እና መስፈርቶች ተግባራዊ ይሆናሉ:-

1. የፌደራል የድህነት ደረጃ (FPL): የፌደራል የድህነት ደረጃ ማለት በዩናይትድ ስቴትስ የጤና እና የሰው ልጆች አገልግሎቶች መምሪያ በፌደራል መዝገብ ውስጥ በየጊዜው የሚሻሻሉ የድህነት መመሪያዎች ናቸው።

2. አጠቃላይ ክፍያ የሚከፈልባቸው ሂሳቦች (AGB):- በዚህ ፖሊሲ መሠረት ለድንገተኛ እና ለሌላ በህክምና አስፈላጊ ለሆነ እንክብካቤ የጤና መድን ላላቸው ታካሚዎች በአጠቃላይ የሚከፈል ሂሳብ አጠቃላይ ክፍያ የሚከፈልባቸው ሂሳቦች ይባላል። የሲዊዲን ጤና አገልግሎት ተገቢ የሆነውን አጠቃላይ ክፍያ የሚከፈልባቸው ሂሳቦች መጠን የሚወስነው ለማንኛውም ድንገተኛ እና በህክምና አስፈላጊ ለሆነ እንክብካቤ ሆስፒታሉ የሚያስከፍለውን አጠቃላይ ክፍያ በ Medicare የሚፈቀዱ ጥያቄዎችን መሠረት ባደረገው ቋሚ መጠን በማባዛት ነው። አጠቃላይ ክፍያ የሚከፈልባቸው ሂሳቦችን የሚዘረዝሩ እና እንዴት እንደሚሰሉ የሚያሳዩ የመረጃ ገፆች የሚከተለውን ድረ-ገፅ በመጎብኘት ሊያገኙ ይችላሉ:- www.swedish.org ወይም ቅጂ ለመጠየቅ በ **1-866-747-2455** መደወል ይቻላል።

3. ያልተለመደ የስብሰባ ድርጊት (ECA)፡- ያልተለመደ የስብሰባ ድርጊቶች የሕግ ወይም የዳኝነት ሂደትን የሚጠይቁ ድርጊቶች ሲሆኑ ዕዳን ለሌላ ወገን መሸጥን ወይም ለአበዳሪ ድርጅቶች ወይም ቢሮዎች ጎጂ መረጃን መስጠትን ያካትታሉ፡፡ ለዚህ ዓላማ የሕግ ወይም የዳኝነት ሂደትን የሚጠይቁ ድርጊቶች፤ ወለድ አግድ፤ የንብረት ሀራጅ፤ የባንክ ሂሳብ ወይም ሌላ የግል ንብረት ማያያዝ ወይም መያዝ፤ በግለሰብ ላይ የፍትሐ ብሔር እርምጃ መውሰድ መጀመር፤ ግለሰብ ላይ እስርን የሚያስከትሉ ድርጊቶች፤ አንድ ግለሰብ ለሰውነት ግንኙነት እንዲጋለጥ የሚያደርጉ ድርጊቶች፤ እና የደሞዝ ስብሰባን ያካትታሉ፡፡

**ማጣቀሻዎች፡-**

| |
|---|
| *የውስጥ የገቢ ኮድ ክፍል 501(r); 26 C.F.R. 1.501(r)(1) – 1.501(r)(7)* |
| *የዋሽንግተን አስተዳደራዊ ኮድ (WAC) ምዕራፍ 246-453* |
| *የተሻሻለው የዋሽንግተን ኮድ (RCW) ምዕራፍ 70.170.060* |
| *የድንገተኛ ህክምና እና የሥራ ሕግ (EMTALA), 42 U.S.C. 1395dd* |
| *42 C.F.R. 482.55 እና 413.89* |
| *የአሜሪካ ሆስፒታሎች ህብረት የልግስና መመሪያዎች* |
| *Providence St. Joseph መድን ለሌላቸው መመሪያ ያለው የጤና ቁርጠኝነት* |
| *የአቅራቢው ተመላሽ መመሪያ፣ ክፍል I ፣ ምዕራፍ 3 ፣ ክፍል 312* |

**ኤግዚቢት ኤ – ሽፋን ያላቸው ተቋማት ዝርዝር**

| **በዋሽንግተን የሚገኙ የስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች** | |
|---|---|
| Swedish Medical Center First Hill/Ballard | Swedish Medical Center Cherry Hill |
| Swedish Issaquah | Swedish Edmonds |

## ኤግዚቢት ቢ - ለስዊዲን የጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች የገቢ ብቃቶች

*የገቢ ውሳኔው የተደረገበት ጊዜ፡- የታካሚው ቤተሰብ ዓመታዊ ገቢ የሚወሰነው የሆስፒታሉ አገልግሎት መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ወይም ማመልከቻው የገባው አገልግሎት ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከሆነ እና ታካሚው የአገልግሎቱን ክፍያ ለመክፈል የመልካም ባህሪይ ጥረቶችን ሲያደርግ ከቆየ ነው፡፡*

| **እንዲህ ከሆነ…** | **ከዚያም …** |
|---|---|
| ለቤተሰቡ መጠን የተስተካከለው ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢ አሁን ባለው የፌደራል የድህነት ደረጃ መመሪያዎች 300 በመቶ ላይ ወይም ከዚያ በታች ነው፣ | ታካሚው የገንዘብ አቅም የሌለው እንደሆነ የሚወሰነው እና የታካሚ ኃላፊነት 100 በመቶ ለተነሳለት የገንዘብ ድጋፍ ብቁ የሚሆነው፡፡[1] |
| ለቤተሰቡ መጠን የተስተካከለው ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢ አሁን ባለው የፌደራል የድህነት ደረጃ መመሪያዎች 301 በመቶ እና 400 በመቶ መካከል ነው፣ | ታካሚው ለታካሚ ኃላፊነት ዋና ሂሳብ 75 በመቶ ቅናሽ ብቁ ነው፡፡ |
| ለቤተሰቡ መጠን የተስተካከለው ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢ ከፌደራል የድህነት ደረጃ 400 በመቶ ላይ ወይም ከዚያ በታች ከሆነ <u>እና</u> ታካሚው ከሲዊዲን ጤና አገልግሎት ሆስፒታሎች በቀደሙት 12 ወራት ውስጥ ለቤተሰቡ መጠን ከተስተካከለው ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢ 20 በመቶ ትርፍ አጠቃላይ የህክምና ወጪ በዚህ ፖሊሲ ስር ለሚገኙ አገልግሎቶች ለሲዊዲን ጤና አገልግሎቶች መክፈል የሚኖርበት ከሆነ፣ | ታካሚው የታካሚ ኃላፊነት ክፍያ መጠን 100 በመቶ የልግስና ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ብቁ ነው፡፡ |

[1] ከ WAC Ch ጋር የሚጣጣም፡፡ 246-453፣ እንደዚህ ዓይነቶቹ ግለሰቦች ለሌላ ሦስተኛ ወገን ሽፋን ስፖንሰርሺፕ ብቁ እንዳልሆኑ ይደነግጋል (RCW 70.170.020(5) እና 70.170.060(5) ይመልከቱ)፡፡